ምርኮን ማርከህ ወደ ሰማይ ዐረግህ።

ሁለት ዓይነት ምርኮዎች አሉ። እነዚህም የሕይወት ምርኮና የጥፋት ምርኮ ናቸው። የጥፋት ምርኮ የሚባለው የእስራኤላውያን በባቢሎናውያን መማረክ ነው (፩ኛ ዜና መዋ.፱፥፩)። እስራኤላውያን ኃጢአትን ቢያበዙ በባቢሎን ተማረኩ። በዚህኛው የምርኮ ሕግ ተማራኪዎች በማራኪዎች ፈቃድ ይኖራሉ። ተማራኪዎች ነጻነት ሳይኖራቸው በባርነት ይኖራሉ። ውሉደ አዳም እኛም በኃጢአት ምክንያት ልጅነትንና ገነትን አጥተን በዲያብሎስ አገዛዝ በሲኦል እስር ቤት እንኖር ነበር። እስራኤል ዘሥጋ የእስራኤል ዘነፍስ ምሳሌዎች ናቸው። ባቢሎን የሲኦል ምሳሌ ነው። ባቢሎናውያን የአጋንንት ምሳሌ ናቸው። እስራኤላውያን በዘሩባቤል አማካኝነት ከባቢሎን ወጥተዋል። ዘሩባቤል የጌታ ምሳሌ ነው። በጠቅላላው በጦር ተሸንፈው፣ በገንዘብ ተገዝተው የሚማረኩት ምርኮ የጥፋት ምርኮ ይባላል። ዲያብሎስ በተንኮሉ ማርኮን የዲያብሎስ ምርኮኞች ሆነን ለ5500 ዘመን ኖረን ነበር። የነጻነታችን አክሊል፣ የሕይወታችን መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እለ ውስተ ሲኦል ፃኡ። በሲኦል ያላችሁ ውጡ። ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ። በጨለማ ውስጥ የምትኖሩ ብርሃን እኔ ሰው ሆኜ አድኛችኋለሁና ውጡ አለን። በዲያብሎስ አገዛዝ የነበርን እኛን እርሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሲኦል አወጣን። የጥፋት ምርኮን ያይደለ የሕይወት ምርኮን ማረከን። በሕይወት ምርኮ ተማራኪዎች ያለፈቃዳቸው በግዴታ የሚያደርጉት ሥራ የለም። ማራኪውም መልካም ፈቃዳቸውን ይፈጽምላቸዋል። በጥፋት ምርኮ የሚጠቀመው ማራኪው አካል ነው። በሕይወት ምርኮ ግን ተጠቃሚው ተማራኪው ነው። ጌታ እኛን ወደ እርሱ ሕይወት ሲማርከን ለእርሱ የተጨመረለት ነገር የለም። እርሱ በባሕርይው ፍጹም ነውና። እኛ ግን በእርሱ በመማረካችን ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከባርነት ወደ ልጅነት ተሸጋገርን። የጌታ ዕርገት ለጻድቃን ዕርገት በኩር ነው። ዐርገ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሓን እንዲል። እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዲስ ተፈጥሮ፣ ለትንሣኤ፣ ለዕርገት በኵር ሆነን። "ወእንዘ ይባርኮሙ ተረኀቆሙ" እንዲል ጌታ ከትንሣኤ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ (ሉቃ.፳፬÷፵፩)። ወደሰማይም ዐርጎ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ (ማር.፲፮÷፲፱)። የእግዚአብሔር ቀኝ የተባለው አምላካዊ ሥልጣን ነው። በዚህ ምድር ሲመላለስ ይራብ ይጠማ ነበር። ከትንሣኤ በኋላ ግን ባለመራብ ባለመጠማት አምላካዊ ግብር ጸንቶ ኖሯልና በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ አለ። መጋቢት ፳፱ ቀን በዕለተ ፅንስቱ ቃል ሥጋ ሲሆን ለቃል ርደት ሲነገር ለሥጋ ዕርገት ይነገራል። መተርጉማን ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ፲፯ን ሲተረጉሙ የቃል ዕርገት በአርባ ቀን የሥጋ ዕርገት በማኅፀን ይላሉ። የሥጋ ዕርገት በማኅፀን መባሉ ሰው አምላክ መሆኑን ያሳውቃል። በዚህ አንፃር የቃል ርደት ሲነገር አምላክ ሰው ሆነ ማለት ነው። ሥጋ በማኅፀን ዐረገ መባሉ የቃልን ገንዘብ ገንዘብ በማድረጉ በድንግል ማኅፀን ተወስኖ ሳለ በኪሩቤል ጀርባ መቀመጡን ግዙፍ ሳለ መርቀቁን መግለጥ ነው። ግዙፍነትን ሳይለቅ ርቀትን ገንዘብ በማድረጉ የርቀት ዕርገት ይባላል። የቃል ዕርገት በአርባ ቀን ማለት በሁሉ ምሉእ የሆነ ቃል ሰውነትን በማኅፀን ገንዘብ በማድረጉ በሥጋ ርስት ወደሰማይ መውጣቱን መግለጽ ነው። ይህ ዕርገት የርቀት ያይደለ የርኀቀት ዕርገት ይባላል። በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ።

በትረ ማርያም አበባው እንደጻፉት